# በዕኩይ ምግባር የተጠመደ ...

ፋኑኤል ከለገሀር
sofiateshome@yahoo.com

በቅርቡ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ የሚል ድርጅት፣ አቶ ዳንኤል በቀለ ለተባሉ ግለሰብ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሠብአዊ መብት እንዲከበር ጥረት አድርገዋል በሚል እንደ ሸለማቸው በድረ ገፁ ይፋ አድርጓል፡፡ ሂውማን ራይት ዎች አቶ ዳንኤል ለሽልማት ያበቃቸውን ምክንያት ግለሰቡ በኢትዮጵያ ሠብአዊ መብቶች እንዲከበሩና ጠንካራ የሲቪክ ማህበረሰብ እንዲፈጠር፣ ሰዎች ሐሳባቸውን በነፃነት መግለፅ እንዲችሉ፣ የሠብአዊ መብቶች ሕጎች ላይ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም ሠውዬው ከእስር ከተፈቱ በኋላም የኢትዮጵያ መንግስት በጎ አድራጐት ድርጅቶችን በሚመለከት ያወጣውን ሕግ “አጣብቂኝ ህግ” በማለት ወቅሰዋል ወዘተ.. በማለት ዘርዝሯል፡፡

እርግጥ ነው በማንኛውም መስክ በጎ ተግባር ያከናወነ ሰው፣ መዘከር፤ መሸለም ይገባዋል፡፡ ሂውማን ራይትስ ግን ከዚህ በተፃራሪው ኢትዮጵያ ውስጥ አፍራሽ ተግባራትን ያከናወኑ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ሲያወድስ ታይቷል፡፡ ሂውማን ራይትስ ዎች የተባለው ሰብአዊ መብት ጠባቂ ነኝ የሚለው ተቋም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ቡድኖች በሚለቃቅመው ወሬ፣ ትክክለኛነቱን እንኳን ለማጣራት ጥረት ሣያደርግ “መንግስት የሠብአዊ መብቶች ጥሰት” ፈፅሟል እያለ ያለመታከት የሚወተውተው እኛ ኢትዮጵያውያን አገራችን ውስጥ የሚካሄደውን እውነታ በቅርበት እየተከታተልነው መሆናችንን እንኳን አስቦት አለማወቁ ምን ያህል የዋኽቀና የዘቀጠ አሰራር እንደሚከተል በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በቅርቡ የሶማሌ ክልልን አስመልክቶ ያቀረበው ሪፖርትና አሁን ደግሞ የሰብአዊ መብት ጀግና አድርጐ የሸለማቸውን ግለሰብ ሁኔታ መመልከት በቂ ነው፡፡

ለመሆኑ ለሠብአዊ መብት መከበር ላደረጉት ጥረት እንደሸለማቸው የነገረን አቶ ዳንኤል ማን ናቸው? በሰብአዊ መብት ዙሪያስ ምን ሰሩ? የሚለውን ላጤነው ደግሞ፣ ድርጅቱ ለሠብአዊ መብት መከበር ፍፁም ደንታ የሌለውና የተለየ ፖለቲካዊ አላማ ያለው መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡

አቶ ዳንኤል ከምርጫ 97 በፊት አክሽን ኤይድ በተባለ የውጭ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ሲያገለግሉ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ደረጃ በየወሩ የሎተሪ አሸናፊ የማግኘት ያህል የሚቆጠር የደለበ ደሞዝ እየተከፈላቸው ሲሰሩ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በደሀ ኢትዮጵያዊያን ስም ተለምኖ የሚመጣን ገንዘብ ምን አልባት መቁጠር እስኪታክታቸው ድረስ በየወሩ ተካፋይ የነበሩ ግለሰብ ናቸው፡፡ ከዚያ በፊትም፣ ያዋጣኛል ያሉትን ማንኛውንም የፍርድ ቤት ጉዳይ ተቀብለው፣ ትርፋቸውን ሲያጋብሱ የኖሩ ጠበቃ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

ግለሰቡ ቅድመ ምርጫ 97 የሚሠሩበት መንግሥታዊ ያልሆነ የውጭ ድርጅት ለሲቪክ ማህበራት በምርጫ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ሲያዘጋጅ አቶ ዳንኤል የአሠልጣኝነት ሥራን ይሠሩ ነበር፡፡ በእነዚህና መሰል አክሽን ኤይድ በሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች ላይ የተለያየ አቋምና አመለካከት ያላቸው ሲቪክ ማህበራት ተወካዮች ስለሚሣተፉ በገለልተኝነት ሁለንተናዊ የመርሕ ግንዛቤ ላይ ያተኮረ ሥልጠና እንዲሰጥ ነበር የሚጠበቀው፡፡ ነገር ግን የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞቹ ላይ አሠልጣኝ ሆነው የቀረቡት አቶ ዳንኤል ይህን አጋጣሚ ከሕግና ከስነ ምግባር ውጭ፣ እርሳቸው የሚደግፉትን ወገን አመለካከት ለመስበክና፣ ለአንድ ወገን የምርጫ ቅስቀሣ ማካሄጃነት ተጠቅመውበታል፡፡ ህብረተሰቡ ይበጀኛል፤ ይሆነኛል የሚለውን በነፃነት እንዳይመርጥ በተለያየ መንገድ ጫና በማሳደር የራሳቸውን የግል አመለካከት ማራመድ ተያያዙት፡፡

አቶ ዳንኤል ከምርጫ 97 በኋላ የተቀሰቀሰውንና፣ ለበርካታ ንፁሐን ዜጎችና ሠላም በማስከበር ሥራ ላይ የተሰማሩ ፀጥታ አስከባሪዎች ሕይወት መጥፋት እንዲሁም በሚሊዮን ለሚቆጠር የመንግስት፣ የሕዝብና የግለሰብ ሐብትና ንብረት ውድመት ምክንያት የሆነው ሁከት ጠንሳሽና አስፈፃሚ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲ አባል ነበሩ፡፡

ለአገራችን ዜጎች የፈለጉት የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊ መሆን ህገ-መንግስታችን በማያሻማ መልኩ ያስቀምጣል፡፡ ይሁንና ግለሰቡ የያዙትን ሥልጣን መከታ በማድረግ በሌሎች ላይ ጫና በመፍጠር፣ ለሁከትና ለብጥብጥ ህብረተሰቡን ያነሳሱ ነበር፡፡ ከላይ የገለፅናቸው በገለልተኝነት፣ መርሕ ተኮር ሥልጠና ሊሠጥባቸው የተዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ፣ የዚህን አባል የሆኑበትን ፓርቲ አቋም በአደባባይ መቀስቀሳቸው ሳያንስ እነዚህን መድረኮች፣ ለሁከትና ብጥብጥ መቀስቀሻነት አውለዋቸዋል፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ በተነሣው ሁከት

በጠንሳሽነትና በአስፈፃሚነት ተጠርጥረው ክስ እንዲመሠረትባቸው ካደረጉት ወንጀሎች አንዱ ይህ ሕገወጥ ድርጊታቸው ነበር፡፡ በዚህ ሕገወጥ ድርጊት ላይ ተሠማርተው እንደነበር ፍ/ቤት ቀርበው ምስክርነት የሰጡት የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል የሚያስታውሱ ሁሉ ያውቁታል፡፡ የፍርድ ሂደቱም የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጠኞች በተገኙበት፣ በእንግሊዝኛና ፈረንሣይኛ ቋንቋ በቀጥታ እየተተረጎመ ስለነበር የአገር ውስጥ የመንግስትና የግል መገናኛ ብዙሃን ብቻ ሣይሆኑ አለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃንም ይዘግቡት ነበር፡፡ በወቅቱ የቀረቡትን የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ የፍርድ ሒደት ዘገባዎች አርካይቭ ውስጥ ሊገኙ ስለሚችሉ በወቅቱ መረጃው ያልደረሳቸው አንብበው ሊረዱት፣ የዘነጉትም ሊያስታውሱት ይችላሉ፣ የተሠወረ ታሪክ አይደለም፡፡

በወቅቱ አቶ ዳንኤል ገንዘብ እየከፈሉ በየአካባቢው ሰዎችን ሁከት እንዲቀሰቅሱና የህዝብ ንብረት የሆኑ አውቶብሶችን እንዲሰብሩ ትዕዛዝ የሰጡዋቸውና  ያሠማሩዋቸውም ምስኪን ሥራ አጥ ወጣቶች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የራሣቸው ፓርቲ አባላትም ቀርበው፣ እራሣቸው አቶ ዳንኤል መስቀለኛ ጥያቄ እያቀረቡላቸው የፈፀሙትን ሕገወጥ ድርጊት ለፍርድ ቤቱ አስረድተዋል፡፡

እንግዲህ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ እኚህን የተለያዩ አመለካከቶች ያሉዋቸው ሲቪክ ማህበራት አባላት የምርጫ ታዛቢነትን ሚና በገለልተኝነት ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ የተሠጣቸውን መድረክ የራሳቸውን የፖለቲካ አመለካከት መስበኪያነትና ሁከት ማነሳሻነት የተጠቀሙ ግለሰብን ነው “የሰብአዊ መብት ጀግና” ብሎ የሸለማቸው፡፡ ምንም ገቢ የሌላቸውን ምስኪን ኢትዮጵያን ወጣቶች ሃምሣና መቶ ብር በመስጠት ደልለው፣ የራሳቸውን አላማ ለማሳካት እርሳቸው የሞቀ ቤታቸው ተቀምጠው፣ ምስኪን ወጣቶችን ሕገወጥ ሁከት ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ፣ ህይወታቸውን አካላቸውን ለአደጋ እንዲያጋልጡ ያደረጉን ግለሰብ ነው ለሰብአዊ መብት መከበር ጥረት ያደረጉ ጀግና ብሎ መሸለሙን ሊነግረን የተነሳው፡፡

ሂዩማን ራይት ዎች አቶ ደንኤል ሰዎች ሀሣባቸውን በነፃነት መግለፅ እንዲችሉ፣ በማህበራት እንዲደራጁ ጥረት ማድረጋቸውን ነግሮናል፡፡ የተለያዩ አመለካከቶች በገለልተኝንነትና በእኩልነት በሚስተናገዱበት መድረክ ነው አቶ ዳንኤል የአንድ ወገን አመለካከትን በመስበክ ለሁከት ማነሳሻነት መጠቀም የጀመሩት፡፡

ህብረተሰቡ የመንግስትና ሌሎች ከእነርሱ አፍራሽ አላማ በተፃራሪ የቆሙ የግሉን ሚዲያ እንዳይከታተል ሌት ተቀን ሲሰሩ የነበሩን ግለሰብ ነው ሂዩማን ራይትስ ዎች "ሰዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልጹ የታገሉ ጀግና" ብሎ ለሽልማት ያበቃቸው፡፡ እረ ለመሆኑ በየትኛው መስፈርት ነው እኚህ ግለሰብ ሃሳብን በነፃነት ለመግለፅ የታገሉ ጀግና ሊባሉ የሚችሉት?

አቶ ዳንኤል ሲፈፅሙዋቸው በነበሩ ሕገወጥ ድርጊቶችና፣ ችግረኛ ወጣቶችን በብር እየደለሉ ሕይወታቸውና አካላቸውን ለአደጋ ለሚያጋልጥ ኢ-ሠብአዊ ምግባራቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦ፣ በግልፅ የፍርድ ሒደት ቅጣታቸውን ተቀብለዋል፡፡ ህዝብና መንግስትን ይቅርታ ጠይቀው ከቃሊቲ እንደወጡ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ሠላማዊ ዜጎች በሙሉ ይህን ያውቃሉ፡፡ ድርጊቶቹንም ለሠብአዊ መብት መከበር እንዳደረጉ ጥረቶች ሳይሆን፣ በሕግም በሞራልም ሚዛን ኢ-ሠብአዊ መሆናቸውን ይረዳሉ፡፡ ኢ-ሠብአዊ ድርጊትን ለሠብአዊ መብት መከበር እንደተደረገ ጥረት ስለቆጠረው ለሠብአዊ መብት መከበር የቆምኩ ነኝ ባዩ ሒዩማን ራይትስ ዎች፣ ምንነት ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ግን ተገቢ ነው፡፡

ይህ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ በፀረ-ዴሞክራ ሃይሎች ሲየሚፈፀሙ ኢ-ሠብአዊ ድርጊቶችን በሚያበረታታ መልክ መንግስት ፈፀማቸው የሚላቸውን መሠረተ ቢስ የሠብአዊ መብት ጥሰት ሪፖርቶች ሲያቀርብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በተከታታይ የዚህ አይነት ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ተራ ልቦለድ መሰል ሪፖርቶችን አቅርቧል፡፡ በቅርቡ በሶማሌ ክልል የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ነኝ ባዩ አሸባሪ ድርጅት የፈፀመውን የሰብአዊ መብት ጥሰት በመንግስት እንደተፈፀመ በማስመሰል ያቀረበውን የሃሰት ሪፖርት በመጥቀስ ብቻ የድርጅቱን ተራነት ማሳየት ይቻላል፡፡

በሶማሌ ክልል የሕዝቡ ፍላጎት መሆኑን ከሚያረጋግጥ ሕገ መንግስታዊ መንገድ ውጭ፣ ክልሉን በኃይል ለመገንጠል የሚንቀሳቀስ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር የተሰኘ ቡድን፣ ህብረተሰቡን እንደሚያምስ ከሁሉም ሠላም ወዳድ ዜጋ የተደበቀ አይደለም፡፡ ይህ መሣሪያ የታጠቀ ሕገ ወጥ አማፂ ቡድን፣ የክልሉ ሠላማዊ ህዝብ ላይ ግድያ፣ ዝርፊያና ወከባ ሲፈፀም መቆየቱ፣ በአዲስ አበባም ለበርካታ ንፁሃን ዜጎች የሕይወት

መጥፋትና አካል መጉደል ምክንያት የሆኑ የሽብር ጥቃቶችን መፈፀሙም የተሠወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በሶማሌ ክልል አቦሌ በተባለ አካባቢ በነዳጅ ፍለጋ ስራ ላይ ተሠማርተው የነበሩ በ60 በላይ  ኢትዮጵያንና ሰባት ቻይናውያን ላይ በተኙበት በሚዘገንን ሁኔታ የፈፀመውም የጅምላ ጭፍጨፋ ከኢትዮጵያንም አልፎ አለም የሚያውቀው ነው፡፡

ታዲያ፣ ይህ የሠብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ የሚለው ሒዩማን ራይትስ ዎች የተባለ ተቋም፣ ኦብነግ የሚፈፅማቸው ድርጊቶች የሠብአዊ መብት ጥሰቶች ሆነው አይታዩትም ይልቁንም አሸባሪ የሆነውን ኦብነግን በቁሳቁስና በስልጠና ከሚረዱት ወገኖች ጐን በመቆም ድርጊቱን ማበረታታቱ የሚያዛዝን ነው፡፡ ይህን ሕገወጥ ታጣቂ ቡድን እና ከጀርባው አይዞህ የሚሉትና ጠመንጃ፣ ጥይትና ፈንጂ የሚያዘንቡ ወገኖች፣ ንፁሃን ኢትዮጵያን ላይ ስለፈፀሙት ኢ-ሠብአዊ ድርጊት አንዴም ሪፖርት አውጥቶ አያውቅም፡፡ ስላልሰማና ስለማያውቃቸው ግን አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ካለው ከውስጥ ከመነጨ ጥላቻ እንጂ፡፡

ከዚህ ይልቅ፣ የክልሉ መንግስትና የፌዴራል መንግስት የፀጥታ አስከባሪዎች፣ በዚህ ኢ-ሠብአዊ ድርጊት ፈፃሚ ቡድን አባላት ላይ የሚወስዱትን የመከላከል እርምጃ ከዕውነት በራቀ አቀራረብ እንደ ሠብአዊ መብት ጥሰት ማቅረብን መርጧል፡፡

ይህ የሒዩማን ራይትስ ዎች አካሄድ፣ ተቋሙ የሠብአዊ መብት ተከራካሪ ሣይሆን ኢትዮጵያ ላይ ሥውር የሆነ አፍራሽ የፖለቲካ አላማን የማራመድ ዝንባሌውን በግልፅ ያመለክታል፡፡ የዚህ አፍራሽ ሥውር የፖለቲካ አላማው ምንጭ በድርጅቱ ውስጥ የተሰገሰጉ ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች መኖራቸው የአገሪቱ ህዝብና መንግስት የሚያደርጉትን መልካም ተግባራት ሊታያቸው አልቻሉም፡፡ ተቋሙ በእጅ አዙር፣ በሠብአዊ መብት ተሟጋችነት ሽፋን የጌቶቹንና የመሠረቱትን መንግስታትና ቡድኖች ዓላማ የሚያስፈፅም ቀኝ እጅ ነው፡፡ ለዚህም ነው ሁሌም ከእውነታ በተፃራሪ በመቆም የጌቶቹን ፍላጐት ለማሟላት ሲጥር የሚታየው፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን በአገራችን ውስጥ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን፣ ጠንቅቀን ስለምናውቃቸው፣ ተቋሙ በየጊዜው የሚያቀርባቸው የፈጠራ ሪፖርቶች፣ የራሱን ምንነት

ከማጋለጥ ያለፈ የሚያመጡት ነገር የለም፡፡ ህብረተሰቡ ይህን ተራ በአሉባልታ የተሞላ ሪፖርት እንደ እውነት ተቀብሎ አገሪቱን ያተራምሣሉ ብሎ አስቦ ከሆነም ተሣስቷል፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን የሚበጀንና የሚሆነንን መንገድ እኛው እራሳችን የመረጥንና የወሰንን ስለሆነ ማንም ጣልቃ እንዲገባብን አንፈልግም፡፡ ያለውን ነባራዊ ሁኔታም በቅርብ ሆነን እያየን ስለሆነ እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያለ ተራ ሪፖርት የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ ሊያውቅ ይገባል፡፡ ለአቶ ዳንኤል በቀለ የተሠጠውም ሽልማት ኢትዮጵያ ውስጥ ሕገ ወጥና ኢ-ሠብአዊ ድርጊት ፈፃሚዎችን ለማበረታታት ለዕኩይ ምግባር የተሰጠ ሽልማት እንደሆነም ጠንቅቅን እንረዳለን፡፡